# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ልዩ እትም ቅጽ 4 ቁጥር 1 ታህሳስ ፩ ቀን ፪ ሺ ፲፪ ዓ.ም.


## የሰላም ኖቤል ተሸላሚነትን ዕድል ይጠቀሙበት

*የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ (https://www.youtube.com/watch?v=AHjUcfm8pyo )*

ታህሳስ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. (December 11, 2019) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የ2012 የኖቤል ሰላም ተሸላሚ በመሆናቸው የተዘጋጀላቸውን ሽልማት በኖርዌ ኦስሎ በደማቅ ዝግጅት ተረክበዋል። እንደ ፖለቲካ ድርጅትነታችን ***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** እንኳን ደስ አልዎ እንላለን። ከ2012 ኖቤል ሽልማት አኳያ የሀገራችን ስም ከፍ ማለቱን፣ ኖቤል ሽልማቱ ከነባራዊው የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታና ከኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ አመለካከት አንፃር መመልከቱ ለምናስተላልፈው መልዕክት ቁልፍ ነውና እነሆ!

"ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የሰው ዘር መገኛ በመሆኗ ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን" በማለት "ኢትዮጵያ ለኛ ተረት ተረት ናት፣ ኢትዮጵያ በኮሎኒ (በቅኝ ግዛት) ይዛናለች፣ ግባችን ከኢትዮጵያ መገንጠል ነው፣ እኛ ኢትዮጵያውያን አይደለንም፣ ወደፊት ኢትዮጵያን እንደ አንድ ጎረቤት ሀገር ነው የምናያት፣ ኢትዮጵያ መበታተን አለባት" ወዘተ. ላሉና እያሉ ላሉ ጥያቄያቸውንና ድርጊታቸውን በሚሳኤል የመቱት የኖቤል ኮሚቴው ሊቀመንበር ተናጋሪ Berit Reiss-Anderson የሀገራችንን ሕዝብ ያስፈነደቀ፣ ኢትዮጵያን ከፍ ያደረገ አባባላቸው ጽንፈኛ ዘረኞችን አንገት ሲያስደፉ ኢትዮጵያውያንን ደግሞ አስጨፍሯል።

"ከዓለም ሀገራት በቅኝ ሳትገዛ ነጻነቷን ጠብቃ የኖረች የዓለም ብቸኛዋ ሀገር፣ ኢትዮጵያ" በማለት አባ ዳኘውን ዳግም ከፍ አድርገዋቸዋል። ኢትዮጵያን ለምትነኩ፣ ምኒልክን ለምትወቅሱ ታሪካችሁን እወቁ ሲሉ በዚህ ዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ድምፃቸውን በማሰማት ኢትዮጵያንና ሕዝብቧን አስፈንጥዘዋል። "ምንሊክ! ጥቁር ሰው"ን ዳግም እንድናዜም አድርገዋል፣ "ጣይቱ እመቤቲቱ"ን በጎሊናችን ቀርጸዋል። ዘርዝረው አይግለጹት እንጂ የዓፄ ዮሐንስ መተማ፣ የአሉላ አባ ነጋ ዶጋሌ፣ የቴዎድሮስ መቅደላ፣ የምኒልክ ዐድዋ፣ የአርበኞቻችንን ተጋድሎ፣ የሠራዊታችን አጥንት በሶማሊያ፣ የወጣቶቻችን ደም በባድመ ወዘተ ወዘተ ዓጽም ለደቂቃም ቢሆን ቀስቅሰዋል።

ኢትዮጵያዊነትን ለማንፀባረቅ በተካነችው አለባበስ ሀገሬ! ሀገሬ! ያዘመረችው ድምጻዊት ለኢትዮጵያ የገደል ማሚቶ ሆናታለች። ዓለም እስኪቀባበላት ድረስ ኢትዮጵያችንን አድምቃለች።

አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችንን በሮምና ቶኪዮ ኦሎምፒክ ማራቶን አቤ ከፍ አድርጎ ያውለበለበውን እስከዛሬ ተተኪ አትሌቶች ምልክታችን፣ መለያችን ረሀብ ብቻ አይደለም ብለው ኢትዮጵያችንን እንዳስጠሩ ወደድነውም ጠላነውም ታህሳስ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. ሰንደቅ ዓላማችን ተውለብልቦ ኢትዮጵያችን ከፍ ብላለች፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶር ዐቢይ አሕመድ አማካኝነት። ጠ/ሚር ዐቢይ አሕመድ እስከ ድክመታቸው እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር የ2019 ሰላም ኖቤል ሽልማት

100ኛው ተሸላሚ ሆነዋል። የዓለም ታሪክ መዝገብ ላይ ሠፍረዋል። ኢትዮጵያን መምራት ሌላ ተመርጦና ተወዳድሮ ማሸነፍ ሌላ።

ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በዚህ የሰላም ኖቤል ሽልማት ያስደመጡትን ንግግር በሀገራቸው ብሔራዊ ቋንቋ አድርገውት ቢሆን ኢትዮጵያን እጅግ ከፍ ባደረጓት። ቢያደርጉት ኖሮ የራሷ ቋንቋና ፊደል ያላት ብቸኛ አፍሪካዊት ሀገር መሆኗን ዝግጅቱን ለተከታተለው 1.5 ቢልዮን ሕዝብ ባስተዋወቋት። "የራስ ወርቅ አያደምቅ" ሆነና መላው የኢትዮጵያም ሕዝብ ዳግም አስተርጓሚ ባላስፈለገው። የበሻሻ ነዋሪዎች መሸለማቸውን ብቻ ሳይሆን ያሉትንም አድምጠ "አይ ጀግና!" ባላቸው፡ ፡ ሌላ የኖቤል ተሸላሚነት ዕድል ካገኙ እንደ ድንቅነሽ/ሉሲ እና ዐድዋ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ተጋድሎ የኖቤል ኮሚቴ ሊቀመንበሯ Berit Reiss-Anderson ወደፊት ያስተዋውቁልን ይሆናል።

የአንድ የሀገር መሪ በማንኛውም ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ በሚያደርገው ንግግር የሀገሩን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልብ ብሔራዊ ቋንቋውም ኩራቱ ሊሆን ይገባል። የቻይና፣ ጃፓን፣ ኮሪያ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ራሺያ፣ የመሳሰሉት ሀገራት መሪዎች በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ የሀገራቸውን መልዕክት በቋንቋቸው የሚያስተላልፉት እንግሊዘኛው ተስኗቸው ሳይሆን ሰንደቅ ዓላማቸውና ቋንቋቸው የሀገራቸው መገለጫ ገጽታዎች፣ ኩራትና ክብራቸው ናቸውና ነው። እና ኢትዮጵያን ያሉ ጠ/ሚሩ ምነዋ ቋንቋዋን ዘንግተው የባዕድ ቋንቋ ወደዱ?

ጠ/ሚር ዐቢይ አሕመድ ያሰሙት ንግግር ጥሩ መልዕክት ያለውና በደንብ የተቀናበረ ቢሆንም ሳንጠቅስ ከዘለልነው "ምኑን ፖለቲከኛ ተሆነ!" ያሰኘናልና ስለ እስረኞች የሰጡት ተሰምቶናል። "ሁሉንም የፖለትካ እሥረኞች ለቀናል" እና ምንም የፖለትካ እስረኛ እንደሌለ ሊያስደምጡ የፈለጉት አንደምታ በየቀኑ ስንቅ እሚያመላልሰው ቤተሰብ ቁስል ላይ እንጨት መሰንቀር አይሆንምን? በተለያዩ አካባቢ የዶር ዐቢይን "ለውጥ" ሳያጣጥሙ ቤታቸው እሥር ቤት የሆኑትን ቤቱ ይቁጠረው። በሀሳብ የተለዩ፣ የፃፉ፣ ተቃዋሚ የሆኑ ሌሎችም ዛሬም በአሸባሪ ስም፣ በመፈንቅለ መንግሥት ስም እየታጎሩ አይደለምን? በቅርቡ ከተፈቱት በመፈንቅለ መንግሥት ሳቢያ የታሠሩ ግለሰቦች እንዳስደመጡን የሚቀርብላቸው ጥያቄ ከታሠሩበት ጉዳይ ጋር ያልተያያዘና የ"ባልደራስ አባል ናችሁ" የሚል አይደለምን?

እንኳንስ ኢሕአዴግ የሚመራው የተሸራረፈ ለውጥ ይቅርና ሥርነቀል ለውጥ የተካሄደበት የደርግ ሥርዓት ሕዝባዊ ድጋፍ ለማግኘት መጠኑ ያነሰ ቢሆንም የዓፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን የፖለቲካ እሥረኞችን በመፍታት፣ በግዞትና በሽፍትነት ለተፈረጁት ምህረት በመስጠት እንደውም ባለሥልጣናቱን በማሠር አልነበረምን የተጀመረው? አዎ! ሥልጣኑን ሲያደላድል የገዳይነቱ መጀመሪያ አድርጓቸዋል። በ1983 ዓ.ም. ወያኔ በኢሕአዴግ ስም ሥልጣን ኮርቻ ላይ ሲወጣ በደርግ ዘመን ሲማቅቁ የነበሩ የፖለቲካ እሥረኞችን መፍታት፣ የቀይ ሽብር ሰማዕታትን አጽም መሰብሰብና አድራጊ ባለሥልጣናቱን ተራቸውን ወደ እሥር ማስገባት ዋናው የድጋፍ ማሰባሰቢያው አልነበረምን? እናማ ጠ/ሚር ዐቢይ "የቀን ጅብ" ያሏቸውን እሽሩሩ እያሉ፤ የነበሩትንም የፖለቲካ እሥረኞች መልቀቅዎ ከላይ ከተጠቀሱት አገዛዞች ሚለይበት ጉዳይ የለም። ሊለይ የሚገባው ሌሎቹ ስልጣናቸውን እስኪያደላድሉ መጠቀሚያ አድርገውት ተራቸውን "የሀሳብ ልዩነት አያሳየኝ፣ ተቃዋሚ አይኑርብኝ፣ እኔ ያልኩት ብቻ ይሰማ" እያሉ ማሠርና መግደል ሲጀምሩ በሀገርና ሕዝብ ስም የማሉ እንጂ ያው ፀረ ዴሞክራሲያዊና አምባገነን አገዛዞች መሆናቸው ነበር። ሆኖም "የለውጥ አራማጁ" ሥርዓት የጥገና ለውጥ አራማጅ ነውና ሥልጣኑም ሳይረጋጋለት ቅጽል ስያሜ እየሰጠ መደብደብና ማሠሩን ተያይዞት "አትቃወሙን፣ አትተቹን፣ እኔን ብቻ አድምጡ፣ መደመርን ተቀበሉ፣ ለብልጽግና ፓርቲ

ድጋፋችሁን ስጡ፣ በትንሹ አሥር ዓመት ልገዛ ተነስቻለሁ" ሲባልልን ወዴት እየተኬደ እንደሆነ ከተረዳነው ውለን አድረናል። በሚገባ ከተረዱት "ትችት" ያልታየዎትን እንዲያዩ፣ የተሳሳቱትን ቆም ብለው እንዲመረምሩ በር ይከፍታል። ቀደምት መሪዎቻችን "እረኛ ምን አለ?" ሲሉ ከብቱን እየጠበቀ፣ ዋሽንቱን እየነፋ የኅብረተሰቡን እሮሮ በእንግርጉሮው ስለሚያስደምጥ ነውና "ሚድያዎች፣ አክቲቪስቶች፣ ምን ይላሉ?" ማለትን አይዘንጉ።

የታህሳሥ 1 ቀኑ የሰላም ኖቤል ሽልማት ለጠ/ሚር ዐቢይ አሕመድ የማስጠንቀቂያ ደወል ነው። ኢትዮጵያ ከፍ ስትል "እልል" እያለ ድጋፍ የሰጥዎ መብቱን ፈላጊ ተቃዋሚ በርካታ ነውና። በውጭም በውስጥም ያለው አብዛኛው ሕዝብ በራሱ አነሳሽነት ድጋፉን በእልልታ፣ በጭፈራ፣ በፈንጠዝያ ሰጥቷቸዋል። ጠ/ሚሩ ገና ሥልጣን እንደተረከቡ የአገኙትን ሕዝባዊ ድጋፍ ከገደል አፋፍ ላይ አድርገው ሲተክዙ ዕድሜ ለኖብል የሰላም ሽልማት ዳግም አግኝተውታል እና ከእንቅልፋቸው ቢነቁ መልካም ነው። ደጋግመን እንደምንለው ሲጀመርም ድጋፉን የሰጥዎ ሕዝብ ከመሠሪው ህወሓት/ወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ አላቀው፤ "ኢትዮጵያ" እያሉ ስሟን እንዳደመቁዋት በተግባር ከዘረኝነት እልቂት፣ ከዘረኛ አከላለል በጥቅሉ ከዘረኛ ሥርዓት እንዲያላቅቁት እንጂ አካሉ በድንጋይ ሲወገር፣ የሰው ልጅ አካል በሜንጫ ሲጨፈጨፍ፣ ንብረት ሲዘረፍ፣ ቤት ሲቃጠል፣ ቤተ ክርስቲያን ሲወድም፣ አዛውንት እናት አባት፣ ሕጻናት፣ ወጣቶች ከኑሯቸው እየተፈናቀሉ ተመልካቻቸው ረሃብ፣ በሽታና ሞት ሲሆን መልሱ "ያለና የነበረ" አይደለም።

ጠ/ሚር ዶር ዐቢይ አሕመድ ሥልጣን ከያዙ ሁለት ዓመት ሊሆናቸው ጥቂት ወራት በቀራቸው ጊዜያት ውስጥ አንዴ እንዳልሰሙ፣ አንዳንዴ በማሾፍ፣ ሲሻቸውም በንዴት የሚያሰሙት ምላሽ ከሕዝብ ያራርቃቸዋል እንጂ  የሚጠቅማቸው አይደለም። ይህ ሕዝብ ይህንን ሁሉ ስቃይ እያየና እየደረሰበት ዛሬም "ሀገሪቷ ሊተካት የሚችል አማራጭ የለም"፣ "የከበዳቸው ጉዳይ ይኖራል" በሚል ተስፋ "እናበረታታቸው" በማለት እንደሆነ ከሰላም ኖቤል ሽልማቱ ሕዝባዊ ድጋፍ ሊገነዘቡ ይገባል። የዛሬ ወር አካባቢ የኖቤል ሽልማት አሸናፊ መሆኖ ከታወቀ ጊዜ አንስተው እንኳ "እስቲ ያሰርኳቸውን ልፍታ፣ የተራቡትን ልመልከት፣ ለተጨፈጨፉት 86 ኢትዮጵያውያን አጣሪ ኮሚሽን ይቋቋምና ወንጀለኞቹን ፍትህ ይመልከታቸው" ከማለት ይልቅ የሌለቦትን የሙታን ዘር ቆጠራ በማሰማት ሀገርን አሳዘኑ። የ86 ወገኖቻችን ዕልቂት ፍትህ እንዲያየው ማድረግና ወንጀለኞችን የመቅጣት ጠቀሜታው ዳግም እንዳይደገም ነበር። ሆኖም ጉዳዩን ከቁብ ሳይቆጠር በመንግሥት ደረጃ መዝለል ነገም ቀን እየቆጠረ ሊከሰት እንደማይችል ዋስትና የለም። እንዲህ ዓይነቱ የሙታን ደም ነው ለተቃውሟችን ድጋፍ፣ ለትችታችን መሠላል የሚሆነው። በምንም መልኩ የንጹሃን ደም በጨካኞች ሲፈስ፣ ሥጋና አጥንታቸው ሲቆራረጥ እንደማየት የሚያም የለም።

እንደ ጠ/ሚሩ የራት ግብዣ ንግግራቸው "የአዲስ አበባ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ፣ የአምቦ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ፣ የጎንደር የጥንታዊ ከተማ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ፣ የመቀሌ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ ፣ የባህር ዳር ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ፣ እንደውም የጅማ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ ሰው እንዴት ከበሻሻ ሊወጣ ይችላል?" ያሉን ከበሻሻ የወጡት "ብቸኛ ጀግና" ሕዝብ ተፈናቀለ ሲሉት አልሰማሁም፣ ሕጻናት፣ አዛውንት፣ ወጣቶች ተራቡ ሲሉት ፓርክ ግንባታ፣ ወገን ሲጨፈጨፍ ዘር ቆጠራ፣ ለድረሱልን ጩኸት በፌደራል የማስደብደብ ምላሽ፣ "አዲስ አበባ የኢትዮጵያ" ሲባል ጦርነት ማወጅ፣ ቤተ ክርስቲያን ሲቃጠል "ያለና ወደፊትም የሚኖር" ባይ ነው አላጋጭ ወይስ ሕዝባችን?

በእርሶ መንግሥት መጠለያ ተሰጥቶት፣ ለዘረኛ ተግባሩ ጥበቃ ተድርጎለት በየአደባባዩ፣ በየሚድያው "በሏቸው፣ ቀንጥሷቸው፣ ያለው ሁለት መንግሥት ነው" ባዩን አሸባሪ ጀዋር መሐመድ የውጭ ዜጋም

ከሆነ ከሀገር ይውጣ አለያም ለፍርድ ይቅረብ ሲባል ምነዋ አዲስ አበባን የሀገር ጥያቄ አደረጉት እስክንድር ነጋና አባላቶቹ ላይ ጉልበቶ በረታ? እውን ለውጭው መንግስታትና ለሰብአዊ መብት ተሟጋች ኃይሎች የባልደራሱ እስክንድር ነጋ ነበር እየተዘዋወረ ጀዋር መሐመድና ቡድኑ በዓለም አሸባሪት መዝገብ እንዲካተቱ መጣር የነበረባቸው፡፡ እውን ከሰላም ተሸላሚው ዶር ዐቢይ ይህ ይጠበቅ ነበርን? ሰሞኑን በአሜሪካ እየተዘዋወረ የሚያደርገውን ጥረት፣ አዎ! የመንግሥትዎ ተቃዋሚም ቢሆን የዴሞክራሲ ግንባታ ላይ ከሆኑ ሌላ ቢቀር መንግሥት በሚቆጣጠራቸው የሚድያ ተቋማት እንዳይዘገብ ሲደረግ አያስተዛዝብምን? ከተጨባጩ የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ከሕዝባችን የዕለት ተለት የስጋትና ሰቀቀን ኑሮ አንፃር የመጣልን "ለውጥ" ሳይሆን "ነውጥ" መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡

አስጊ የመበታተን አደጋ ላይ ያለችውን ኢትዮጵያ ለማዳን ጥረት ማድረግ፣ በሚልዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን መፈናቀልና መጠለያ፣ ምግብ፣ ህክምና እጦት ነው ቅድሚያ የሚሰጠው ወይስ እድገትና ልማቷን ብንወድም ብስኪሌት ማስጋለቢያ ፓርክ? እውን እንነጋገር ከተባለ ሌላውን እንተወውና የአዲስ አበባ ሕዝብ የቸገረው ብስኪሌት መጋለቢያ ነውን? ወይስ ወደፊት ሀገራችን ወደ አላስፈላጊ የእርስ በርስ ግጭት ከገባች በመከላለል ስም ሊወሩን ላሰፈሰፉ ባዕዳን ቱጃሮችና ልጆቿቸው ከአሁኑ መዝናኛ መዘጋጀቱ ነው? ቢባል አያስደንቅም። ቤተ መንግሥቱም በገንዘባቸው ተዘጋጅቶላቸዋልና። ቤተ መንግስቱ ላይ፣ አዲስ አበባን የማስዋብ ሥራ ላይ የሚፈሰው ነዋይ ሚላስ ሚቀመስ አጥተው ለተከራመቱና ሞት በየቀኑ ለሚረከባቸው ወገኖቻችን የነፍስ አድን አጣዳፊ ተግባር ላይ ቢውል አይመረጥምን? ሲደላን ፓርኩንም፣ ሽርሽሩንም እናገኘዋለን፡፡ ምነዋ መከናነብ አማረ?

አዲስ አበባን የማስዋብ ሥራም ከዚህ በፊት የዛፍ ተከላ ፕሮግራሙን በተመለከተ እንደጠቆምነው እርሶም ሆኑ ሌሎች ባለስልጣናት የበላይ ሃላፊ ቢሆኑም የማጥናትና የማስፈፀሙን ሥራ ግን በከተማ ፕላን ባላሙያዎችና በመሃንዲሶች መከናወን እንዳለበት ልናሳስብ እንወዳለን፡፡ የአዲስ አበባ መሠረተ ልማት ችግር በረጅም ጊዜና ቀጣይነት ባለው ዕቅድ መቀረፍ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ የፍሳሽ ማስተላለፊያ ሥራዎች፣ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎቶች፣ የመንገድና ትራንስፖርት ችግሮችና፣ የቆሻሻ አሰባሰብ የከተማዋ ኗሪውን ለበሽታ ያጋለጡና መፍትሔ የሚፈልጉ አስቸኳይ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ለብዙ አሥርተ ዓመታት በቸልተኝነት የታለፉ ችግሮች በባለሙያዎች ሊሠራባቸው ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን ከተማዋም እየተዋበች ትመጣለች፡፡ ስለዚህ ጥቂት "የተዋቡ" ፓርኮች ላይ ከማተኮር ከተማ አቀፍ መሠረተ ልማት ላይ መረባረብ ይበጃል እንላለን፡፡ በተጨማሪም በሚሠሩ መሠረተ ልማቶች አኳያ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ አብሮ ካላደገ ፓርኮች፣ መናፈሻዎች መልሰው ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ቀላል ነው፡፡ ቆሻሻ መጣያ፣ ፍሳሽ ማሶገጃ፣ የተሟላ ሽንት ቤት የሌለው መንደርና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (ሆቴል ቤት፣ ሱቆች፣ ፑቲኮች፣ ቡና ቤቶች፣ የንግድ ተቋማት እና ሌሎች) ቆሻሻውንም ለማስወገድ፣ ለፍሳሹም ቀዳዳ ለመፈለግ፣ ለሽንት ቤት መገልገያም እንደተመቻቸው ይሆናልና ቅድሚያ ትኩረት ካልተሰጠው አስዋብን፣ ገነባን፣ ተከልን ያልነው መልሶ ለሌላ ወጪ መዳረጉ አይቀርም፡፡

ጠ/ሚር ዐብይ አሕመድ የኖቤል ሽልማቱን አስመልክቶ በቤተ መንግሥት በተደረገው የእራት ግብዣ ላይ ባሰሙት ንግግር ለሀገራችን ችግር ሕዝቡን ተጠያቂ ሊያደርጉ ደፍረዋል፡፡ እጅግ አሳዛኝ፡፡ "እግዚአብሔር የሚሠጠውን ሁሉ ሰጠን ግመሥገንና መሥራት ስለማናውቅ ነው ለማኝ የሆነው" ይሉናል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡፡ በትንሹ ለአለፉት ሃምሳ ዓመታት በተፈራረቁበት ገዳይና ሌባ አገዛዞች ልጆቹን ከመገበር አልፎ ስብህናውን ያጣ፣ እንደ በሬው ተለጉሞ ያለውን ሕዝባችንን ሲወቅሱ እንደሚያመን ቢረዱ ጥሩ ነው፡፡ እየተደበደበ፣ እየታሠረ፣ እየተገደለ፣ እየተሰደደ ይችን ሀገር ጠብቆ ያለው በእግዚአብሔር ቸርነት እርሶ ሳይሆኑ ሕዝባችን ነው፡፡ አንዳንዶች እየገደሉ "ወርቅ ሲያነጥፉለት

ፋንድያ ባይ ሕዝብ" ሲሉት፣ ወያኔና ሻቢያ "የመቶ ዓመት ታሪክ" ብለው ሲያንቋሽሿት፤ ዛሬም የዘርና ቋንቋ ክፍፍሉ እጅግ ጠዞ ሀገሬ እያለ የሚጮህላት መላው ሕዝባችን መሆኑን ለተረዳ "ሥራ የማይወድ፣ ወሬኛ" አድርገን ስንስለው ያሳዝናል። ችግሩ ያለው 28 ዓመት በኢሕአዴግ ስም የተሰገሰጉት የቀን ጅቦችና አሁንም በለውጥ ስም እየተገላበጡ አሉት ባለሥልጣናትና ዘራፊዎች ጋ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ "አትቃወሙን፣ አታብጠልጥሉን፣ አትተቹን" ሲሉም ተደምጠዋል። እርሶ ለሀገርና ሕዝብ ሲሉ ሕዝብ ሲጠይቅ "አልቃሻ" ከማለት ለምላሹ ይዘጋጁ። ተቃዋሚን፣ የሀሳብ ልዩነትን የሚያሸንፉት ከቀን ጅቦች፣ ከአሸባሪ ዘረኞች፣ ከገደል ከታች አድርባይ ምሁሮች ጎን ተሰልፈው ሳይሆን ከወደድዎና ከሚወድዎ ሕዝብ ጋር ነውና የሰላም ኖብል ሽልማቱን ዕድል ይጠቀሙበት። አሁንም ቅድሚያ ሀገራችን! ቅድሚያ ሕዝባችን! እንላለን።

ከዚህ በዘለለና በድብቅ ተልዕኮ ለባዕዳን ተንበርካኪ በመሆን በልማትና ዕድገት ስም ኢትዮጵያን አዳክሞ ለመሸጥ፣ ሕዝባችንን ከፋፍሎ ስብህናውን እንዲያጣና የባዕድ ተገዥ ለማድረግ የሚወጠን ደባ የትም እንደማያደርስ በእርግጠኝነት ልንናገር እንችላለን። ***ይህ የሰላም ኖቤል ሽልማት ኢትዮጵያ ላይ እየተካሄደ ያለውን የዘር ማጥፋት ጥቃት ሊያስቆሙበት፣ ተዋዶና ተፈቃቅሮ የኖረውን እስላምና ክርስቲያን ይበልጥ ሊያስተሳስሩት፣ ሕዝባችንን ከረሀብ፣ በሽታና፣ ድህነት ሊያላቅቁት፣ የዘርና/ቋንቋ አከላለልን ብሎም ዘረኛውን የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት በኢትዮጵያዊ ሕገ መንግሥት ሊቀይሩት ሥልትና ዘዴ ካልቀየሩ ለኢትዮጵያችን የሚደረገው ጩኸት እርሶና አገዛዞን እንደሚውጥ ሊረዱት ይገባል። ለባዕድ ተገዥ ሁነን የምናገኘው እድገትና ልማት በአፍንጫችን ይውጣ። መልካም መሠረት ያለው አገዛዝ ከሕዝብ ከመጣ ደህነታችንን ለመቅረፍ፣ ኢትዮጵያችንን ከፍ ለማድረግ እኛው በቂ ነንና ይህንን ሕዝባዊ ትህትና ይጠቀሙበት።***

በአዲስ አበባ በተካሄደው የድጋፍ ሰልፍ የኦሮሞ ልጆችና ፈረሰኞች ያሳዩት ጭፈራና ድጋፍ ለሚገባው ኦሮሞ ለኢትዮጵያ ያለውን ፍቅር ያንጸባረቀበት ነው። "እኛ ለኢትዮጵያችን" የሚል ቲ ሸርት ለብሰው ጭፈራውን ያደመቁት እነሱ ናቸው። ዘር፣ ሃይማኖትና ዕድሜ ሳይለይ በተሰጠዎ የጋራ ድጋፍ ሁሉም ኢትዮጵያዊ፣ ሰንደቅ ዓላማውን እንደሚወድ፣ አንድነቱን እንደሚፈልግ ገንፍሎ የወጣው ሕዝብ እየነገርዎ ነውና ያድምጡት።

በሌላ በኩል በቅርቡ ሥራ ላይ እንዲውል ያቀረቡትን የመደመር ፍልስፍና እና የኢሕአዴግ ወደ ብልጽግና ፓርቲ መሸጋገር የኢትዮጵያን ችግር ይፈታል ማለት እራሱን የቻለ አነጋጋሪ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን። የነበረን ሕብረት ወደ ፓርቲ መቀየር ሳይሆን የነበረን ዘረኝነት ወደ ኢትዮጵያዊነት መቀየሩ ላይ ነው ቁልፉ። አለያ ነገሩ ሁሉ "አዘለም አንጠለጠለ ያው ተሸከመ" ነው። በዚህ ጉዳይ እንደ መንግሥት አካልና እንደ ኢሕአዴግ አባልነት ከህወሓት በቀር ሁሉም ድርጅቶች በግለሰብ ጭምር ደግፈውታል። ባናምንበትም ይህ በኢሕአዴግ ድርጅቶችና አባላት አብላጫ/ሙሉ ድምጽ የጸደቀውን የመደመር ፍልስፍና እና የብልጽና ፓርቲን ምሥረታ የመከላከያ ሚንስትሩ አቶ ለማ መገርሳ መቃወማቸውን አሳውቀዋል። የመቃወም መብታቸው እንደተጠበቀ አንድ የመንግሥት አካል ያውም መከላከያ ሚንስትር እንዲህ ዓይነት አቋም ሲወስድ እራሱን ከያዘው መንግሥታዊ የኃላፊነት ቦታ ማንሳት ይኖርበታል፤ ግና አቶ ለማ አላደረጉትም። በመሆኑም ከጠ/ሚር ዐብይ አሕመድ መንግሥት ፕሮግራም፣ ፖሊሲ በተፃራሪው የቆመ ባለሥልጣን አብሮ ሊጓዝ አይችልምና ጠ/ሚሩ ያለምንም ማቅማማት አቶ ለማ መገርሳን ከሥልጣናቸው ማንሳት ተገቢ ነበር፤ ግና እስካሁን ተግባራዊ አላደረጉትም። እዚህ ላይ ነው ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ፈጣን ፖለቲካዊ ውሳኔ መስጠት ይሳናቸዋል የሚባለው።

**በመጨረሻም የሰላም ኖቤል ሽልማቱን ማሸንፍዎ ከተሰማ እንኳ በነበሩት ሁለት ወራት እጅግ አሳዛኝ ጉዳዮች በእርሶ ቸልተኝነት፣ ቆራጥ አመራር አለመስጠት፣ ሌሎች እንደሚሉት "ከአቅሞ በላይ ሆኖ" ወይም ሆን ብለው የሚጓዙበት አቅጣጫ ያሳዝናል። የትላንቱ ኖቤል ሽልማት ክብረ በዓል ነው። እውን ቀና ጉዞ ከፈለጉ ትላንት ላጠፉት አባባል፣ አካሄድ ሕዝባችን እየተቃወመ ደግፎቷል፣ አጨብጭቦሎታል፣ እልል ብሎለታልና ለራሶ ብለው ቢጣፍጡ ጥሩ ነው። በአግባቡ ለሕዝብ ድምጽ ጆሮ ሰጥተው የሁሉም ዘር/ነገድ/ጎሳ/ብሔር/ብሔረሰብ ክልል ኢትዮጵያ ማድረጉ ላይ ቁርጠኛ አቋም ወስደው ይህንን ሕዝባዊ ድጋፍ ካልተጠቀሙበት "ከሀገራችን እንጂ ከርሶ ምናለን" ባይ ጊዜ እንዳይመጣብዎ ልንጠቁም እንወዳለን።  ይህንን የሰላም ኖቤል ሽልማት ባለመጠቀም ሀገራችንን እንዳያሳፍሯት ይጠቀሙበት እንላለን። ቅድሚያ ኢትዮጵያችንን እንፈልጋለን። "እየዬ ሲዳላ" ነውና እኛ እየተተራመስን ጅቡቲ፣ ኬንያ፣ ሱዳን፣ ኤርትሪያ ሌሎችም ቀና ጉርብትናቸውን ብንፈልግም ቅድሚያ መስጠት ያለብን ለግማሽ ምዕተ ዓመት ለተጎሳቆለው ሕዝባችን ነው። ሕዝባችን ቆሞ ሲሄድ፣ ሀገራችን አንድ ስትሆን ነው ከምሥራቅ አፍሪካ አልፎ አፍሪካን በአንድ ሰንሰለት ልናስተሳስር የምንችለው። መንግሥት ይመጣል፣ መንግሥት ይሄዳል ኢትዮጵያና ሕዝቧ ግና ለዘላለም ይኖራሉ።**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!**
***ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!!!***
**"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"**
**ታህሳስ** 04 **ቀን** 2012 **ዓ.ም**. (December 14, 2019)

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጬት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin